# ወርሃዊ የአየር ጠባይ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከማርች 1-31/2023 የነበረው የአየር
## ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከኤፕሪል 1-30/2023 የሚኖረው የአየር
## ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2023
አዲሰ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ....................3

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....................5

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....................6

ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው....................7

ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....................7

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ....................8

ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ....................8

ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....................8

እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....................9

ካርታ 13 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....................9

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር....................10

ጠባይ አዝማሚያ ....................10

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....................11

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....................12

# እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች ወር የዝናቡ ስርጭት ከደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ወደ መካከለኛው፣ ምስራቅ፣ ሰሜን ምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ቀስ በቀስ እየተስፋፋ በመሄድ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚዳርስበት ወቅት ነው፡፡


ባለፈው ማርች ወር የመጀመሪያው  አስር ቀናት የዝናቡ ስርጭት በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ተወስኖ የነበረ ሲሆን፤ በሁለተኛው አስር ቀናት ግን በከባቢ አየር ውስጥ የነበረው እርጥበታማ የአየር ሁኔታ በተሻለ መልኩ በመጠናከሩ በአብዛኛው የሀገሪቱ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚዎች ላይ ተስፋፍቶ ታይቷል። በተለይም በመጠንም ሆነ በሥርጭት ረገድ ተስፋፍቶና ተጠናክሮ የነበረ በመሆኑ  በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍና የወንዞች መሙላት ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው፡፡ በሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የምስራቅ፣ የመካከለኛው፣ የደቡብ ምዕራብና የሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ ጥሩ የሚባል ዝናብ ነበራቸው፡ ስለሆነም ባለፈው የማርች ወር ለበልግ ዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች የተጠናከሩ ስለነበሩ አብዛኛዎቹ የምሥራቃዊ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎቹ የተስፋፋ ዝናብ አግኝተዋል። በዚሁ መሰረትም በወሩ ዉስጥ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 51.0፣ 41.4፣ 31.0፣ 51 በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 37.0፣ በድሬዳዋ 47.0፣ በመተሃራ 39.1፣ በአደሌ 33.6፣ በአምቦ 49.0፣ በባቲ 34.5፣ በደሴ 43.2፣ በደምቢ ዶሎ 38.6፣ በመሃል ሜዳ 35.8፣ በጭፍራ 104.0፣ 51.0፣ 42.0 እና 30.4፣ በዳሊፋጊ 88.0ና 107.4፣ በቡርጂ 34.8፣ በአማን 62.6፣ በሜጋ 35.0፣ በወላይታ ሶዶ፣ 40.3፣ 45.5 እና 49.3ና 43.2 በወሊሶ 35.6፣ በሰመራ 46.0፣ በዱብቲ 71.0፣ በሻምቡ 35.5፣ በሳውላ 71.1፣ 98.6 እና 34.6 በነቀምቴ 56.2፣ በሚሌ 50.0፣ በሞያሌ 43.5 እና 32.8፣ በመኢሶ 50.0 እና 30.2፣ በመተሃራ 33.0፣ 37.6፣ በምዕራብ አባያ 44.0፣ በቀብሪደሃር 30.0 እና 44.8፣ በደገሀቡር 31.1፣ በገዋኔ 30.4 እና 34.0፣ በፊቅ 150.0፣ 130.0 እና 94.3፣ በገለምሶ 36.2፣ በኤሊዳር 30.7፣ በእነዋሪ 36.0፣ በዱብቲ 71.0፣ በዲላ 30.8፣ በዶሎመና 30.5፣ በድሬዳዋ 33.4፣ በቦሬ 82.0፣ 32.1 እና 33.0፣ በብላቴ 45.1፣ በቡኢ. 45.5፣ በባቲ 32.0 እና 35.0፣ በአዋሽ አርባ 55.0 እና 30.0፣ በአደሌ 39.2፣ በሀሮማያ 36.6፣  በአቦምሳ 48.4፣ በያቤሎ 66.5፣ በሞያሌ 88.8፣ በአርባ ምንጭ 65.6፣ 52.2 እና 47.7፣ በነገሌ 65.6 እና 33.7፣ በሀረሪ 58፣ በማጂ 53.7፣ በጂንካ 40.2፣ በሆሳዕና 32.2፣ በጅማ 49.5 እና 47.0፣ በቦሬ 46.5 እና 32.7፣ በዝዋይ 40.0፣ በእንድብር 37.2 እና 30.2፣ በወራቤ 34.5፣ በመተሃራ 32.8፣ በኮንሶ 30.7፣ በሂርና 79.3፣ በስሪንቃ 76.9፣ በሀዋሳ 34.8፣ በሊሙገነት 30.4፣ በጃራ 35.2 እንዲሁም በቀብሪበያህ 30.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

በሌላ በኩል የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በሀገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ላይ ማለትም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ40 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ ተመዝግቦዋል፡፡ ከ40 ዲ.ሴ በላይ የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል በፉኚዶ 42.0፣ 41.0 በላሬ 41.0፣ በጋምቤላ 41.0፣ በአቦቦ 40.2፣ 41.2 እና 42.0፣ 41.0፣ በመተማ 40.6፣ በአሊያ 40.6 40.0 በጎዴ 41.6፣ 41.2፣ 41.4፣ 42.0 እና 42.2፣ በጋምቤላ 41.6፣ 41.8፣ 43.8 ፣ 41.0፣ 42.5 እና 43.5፣ 43 እንዲሁም በመተማ 40.5፣ 40.8፣ 41 እና 42.2 ዲ.ሴ የደረሰ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን እንደተመዘገበ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ይጠቁማሉ።


ባለፈው የማርች ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከአማራ በደቡብ ጎንደር፣ በምስራቅ ጎጃም፣ በደቡብና ሰሜን ወሎ፤ ከጋምቤላ የማጂንክ ዞን፤ በአፋር፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፤ በአዲስ አበባ፤ በሶማሌ፤ በድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ25-379 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ5-22 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 9 እና 10) ፡፡

ባለፈው የማርች ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ በምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ ጎንደር ኪስ ቦታዎች፣ በደቡብና ሰሜን ወሎ፤ በአፋር፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ ከኢሉአባቦራና ከምዕራብ ወለጋ በስተቀር በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፤ በአዲስ አበባ፤ በሶማሌ፤ በድሬዳዋና ሀረሪ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ የተቀሩት የምዕራብ አማራ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝና የጋምቤላ ክልል ዞኖች ላይ እንዲሁም በኢሉአባቦራና በምዕራብ ወለጋ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመደበኛው በታች የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 11) ፡፡


ካርታ 9 ኢ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 10 ኢ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የማርች ወር አብዛኛዎቹ የምሥራቃዊ አጋማሽ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተስፋፋ እርጥበት አግኝተዋል። ይህም ሁኔታ በተለይም የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲኖራቸው ያስቻለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የማሳ ዝግጅት ለማድርግ እና የተለያዩ ሰብሎችን ለመዝራት አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ወቅት ሰብሎችም ሆነ በአካባቢዎቹ ለሚበቅሉ ቋሚ ተክሎች በጎ ጎን ነበረው። በተጨማሪም ከመጀመሪያው አስር ቀን በኋላ ወደ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሃገሪቱ ስፍራዎች ተስፋፍቶ የነበረው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውኃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት በጎ ጎን ነበረው። በአንፃሩም በብዙ ሥፍራዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ መጠኑ ከ30 ሚ.ሜ የበለጠ ከባድ ዝናብ የነበራቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተገኘው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በተለይም ውሃ አጠር ለሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍና የወንዞች መሙላት ሊያስከትል በመቻሉ በእንሰሳት፣ በሰዎችና በንብረት ላይ እንዲሁም ቀደም ብለው በተዘሩትና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙት ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ40 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን፤ ይህም የነበረው ፀሐያማና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ በአካባቢው ከነበረው የእርጥበት እጥረት ጋር ተዳምሮ በወቅቱ አጠቃላይ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ እንዲሁም በአርብቶ አደሩ አካባቢ የእንሰሳት መኖና ውኃ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረዉ (ካርታ 12)፡፡


ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ማርች ወር የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ አብዛኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ የመካከለኛው ምስራቃዊ አባይ እና አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው ናቸው፡፡ የተቀሩት አብዛኛው ዋቢሸበሌ፣ ኦጋዴን፣ አባይ እና ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ እንደነበር የተተነተኑ የውኃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 13) ፡፡

ካርታ 13 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች መጠናከር ጋር ተያይዞ የኤፕሪል ወር ከተቀሩት የበልግ ወራት አንጻር በተሻለ ሁኔታ የዝናቡ መጠንና ሥርጭት በብዙ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ እየተስፋፋና እየተጠናከረ የሚሄድበት ወር ሲሆን፣ በተጨማሪም በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

በመጪው ወር ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የከባቢ አየር ሁኔታዎች (Atmospheric conditions) እንደሚጠናከሩና ከዚህም ጋር ተያይዞ ከቀደሙት ሁለት የበልግ ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ሆኖም ግን ከበልግ ዝናብ የመዋዠቅ ባህርይ የተነሳ ተከታታይ ደረቃማ ቀናት በወሩ ውስጥ ሊከሰት እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ <u>ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ አርሲና ባሌ፣ ቦረናና ጉጂ፤ የሐረሪ ክልል፤ ድሬዳዋ፤ አዲስ አበባ፤ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች! ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ"ሰሜን ሸዋ እንዲሁም ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ አንዳንድ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ ከአፋር ዞን 3፣ 4 እና 5፤ ከትግራይ ክልል የመካከለኛው፣ የምሥራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች እንዲሁም ጥቂት የምዕራብ ትግራይ ዞን ቦታዎች፤ ሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልልና አንዳንድ የሶማሌ ክልል ዞኖች በአብዛኛው ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በተለይም በሰሜን ምስራቅ፤ በምስራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚኖረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችት የተነሳ በአንዳንድ ሥፍራዎች በተለይም በምስራቅና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከባድ ዝናብ የመኖር ዕድሉ የሰፋ ነው። የዝናብ መጠኑም አብዛኛውን ጊዜ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ሊሆን እንደሚችል የሚጠበቅ ቢሆንም፤ በጥቂት ሥፍራዎች ላይ ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በሌላ በኩል የሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።</u>

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የኤፕሪል ወር ከቀደሙት ሁለት የበልግ ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እርጥበታማ ሁኔታ (Moist condition) በብዙ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፣ በተለይም ከማርች ወር መግቢያ ጀምሮ በተከታታይ ቀናቶች እርጥበት እያገኙ በነበሩ ስፍራዎች ቀደም ብለው ለተዘሩና በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች እንደሚኖር የሚጠበቀው እርጥበታማ ሁኔታ በደጋማው አካባቢ ለሚዘሩ ሰብሎችም ሆነ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት የግጦሽና የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በተለያየ ምክንያቶች የበልግ ወቅት የእርሻ እንቅስቃሴን ዘግይተው ለጀመሩና የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የሚጠበቀው እርጥበት አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥረ ከግምት በማስገባት በቂ ግብአቶችን ለመጠቀም ከወዲሁ ዝግጅት እንዲያደርጉና ከበልግ ዝናብ የመዋዠቅ ባህርይ የተነሳ ተከታታይ ደረቃማ ቀናት በወሩ ውስጥ ሊከሰት ስለሚችል እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን እርጥበት ከግምት  በማስገባት በመካከል ለሚከሰቱ ደረቅ ሰሞናት ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችል የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብና ለማከማቸት የሚያስችሉ ተግባራትን አስቀድሞ ለማከናወን ዝግጅት እንዲደረግ ይመከራል፡፡ በሌላ መልኩ በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛውና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል በትንበያው የተመለከተ ሲሆን፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊፈጠር ስለሚችል አርሶ አደሮች ጎርፎችን መደበኛ መፋሰሻቸውን ተከትለው እንዲፈሱ የማድረግ ተግባራትንና በተለይም አንዳንድ አካባቢዎች በተከታታይ ከነበረውና ከሚጠበቀው በጣም እርጥበታማ ሁኔታ ጋር በተያያዘ በተለይ ውሃ ገብና የአፈር ፀባያቸው በቀላሉ ውሃውን በማያሰርግባቸው አካባቢዎች ባሉ ማሳዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛትን ሊያስከትልና በማሳዎች ላይ ውሃ እንዲተኛ ሊያደርግ ስለሚችል ተገቢው ትኩረት ተደርጎ የበዛውን ውሃ በቀላሉ ለማጠንፈፍና ለማስወገድ የሚያሰችሉ ዘዴዎችን ከወዲሁ ሊተገብሩ ያስፈልጋል፡፡

# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል1 እስከ 30/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የኤፕሪል ወር ከተቀሩት የበልግ ወራት አንጻር በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ በቦታም ሆነ በመጠን የተሻለ እርጥበት የሚገኝበት ጊዜ ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያየዞ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ውስጥ የሚገኙ ግድቦች፣ ወንዞች እንዲሁም ሌሎች የውሃ አካላት የተሻለ የውኃ መጠን እንዲኖራቸው ከማስቻል አንጻር ከፈተኛ ትርጉም የሚሰጠው ወር ነው።

በተሰጠው የአየር ጠባይ ትንበያ መሰረት በመጪው የኤፕሪል ወር የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች አሁን እየተስተዋለ ያለው እርጥበት በመጠንም ሆነ በስርጭት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ እየተጠናከረ እንደሚሄድ ይጠበቃል፡፡ በዚህም መሰረት አብዛኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥሸለቆ፣ አባይ፣ አዋሽ፣ የታችኛውና የመካከለኛው ተከዜ፣ እንዲሁም የላይኛውና የመካከለኛው አፋር ደናክል እና ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ለገፀ-ምድር እና ለከርሰ-ምድር የውሃ ሀብት መጎልበት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን በአንዳንድ አካባቢዎቾ ላይ ሊከሰት ከሚችለው ከባድ ዝናበ ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎቻው ላይ በንብረት እና በህይወት ላይ ጉዳት ለማደረስ የሚችል አቅም ሊኖረው ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት ከቅጽበታዊ ጎርፍ ክስተትም ሆነ ከወንዞች ሙላት ጋር ተያይዞ በሚከሰት መጥለቅለቅ በንብረትም ሆነ በሰወ ህይወት ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳትን ለመቀነስና ብሎም ለማስቀረት የሚያስችሉ ዝግጅቶችን ማለትም የውሃ መፋሰሻ ቦዮችን ማዘጋጀትም ሆነ ከከፍታ ቦታ የሚወርድ የውኃ ፍሰት ፍጥነትን የሚገታ መከላከያ (Flood Breakers) እንዲኖራቸው ማድረግ የሚመከር ሲሆን፤ በተለይም በተዳፋት አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ከወዲሁ አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ማሳሰብ እንወዳለን፡፡ በአንጻሩ ግን ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በመጪው ወር የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለዘለቂ የውሃ ፍጆታ ለማዋል የተለያዩ ዘዴውች በመጠቀም ውሃ የማሰባሰብ በተገቢው ሁኔታ የማጠራቀምና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ በአጽንዖት ይመከራሉ፡፡